# የ‹‹እናውቅልሃለን›› የፖሊቲካ ፍልስፍና ውጤት!

*ዮሴፍ ሙሉጌታ ባባ, PH.D.* 06-13-17*

‹‹የሕዝባችን ብሶትና የድሆች አሰቃቂ ሁኔታ እስከ አጥንታችን ድረስ ዘልቆ ተሰምቶናል›› ያሉን ‹‹ምርጥ የኢትዮጵያ ልጆች››፣ የ‹‹እናውቅልሃለን›› ፖሊቲካዊ ፍልስፍና ማራመድ ከጀመሩ እነሆ 42 ዓመት አስቆጠሩ። ከዛ ጊዜ ወድህ የ‹‹እናውቅልሃለን›› ፖሊቲካዊ ፍልስፍና በሀገራችን ባሕል ሆኖ ቆይቷል።

(1) በአንድ በኩል፣ አብዮታዊ መንግስት የመሰረቱ ‹‹ቡዳዎች›› ተነስተው ለሰፊው ሕዝብ መቆማቸውን አበሰሩን። የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ አብዮታዊው መንግስት ከፊውዳሉ መንግስት ፈጽሞ የተለየ መሆኑን ስሰማ፣ ጮቤ መርገጥ ጀመረ። እነኝህ ግለሰቦች፣ ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል እንደሚኖር ለሰፍው ሕዝብ ቃል የገቡት፣ በኮምቶ ሥላሴ ስም ምሎ ሳይሆን፣ ‹‹የአብዮቱ ሰይፍ አንገታችንን ይቀንጥስ›› በማለት ነበር። የአብየቱ ሰይፍ ወድያውኑ መቀንጠስ የጀመረው ግን፣ የሕዝቡን አንገት እንጅ የ‹‹ቡዳዎቹ››ን አልነበረም! የ‹‹እነውቅልሃለን›› የፖሊቲካ ፍልስፍና ከቀመሩ ‹‹ቡዳዎች›› መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑ ጅቦች ነበሩ። አብዮቱ በጅቦች እንደ ተጠለፈ የገባት ሄለን መሃመድ፣ ትዝብቷን እንድ ስትል አስፍራ ነበር፡-

አብዮት አብቦ—ጎምርቶ አሽቶ<br>
የሚዘነጥፈው—የሚቆርጠው ጠፍቶ<br>
ጅቡ በላው አሉ—ሌት ከማሳው ገብቶ

አብዮቱን ከጅቦች ማጥራት አልተቻለም ነበር። ሆድና ጅብ የአንድ ስሙኒ ሁለት ገጽታ በመሆናቸው፣ ለድሆች አሰቃቂ ሁኔታ ቁብ የሰጠ አልነበረም። የ‹‹እናውቅልሃለን›› የፖሊቲካዊ ፍልስፍ ‹‹የግል ጥቅምን ብቻ ማሳደድ›› በሚል የጅቦች አስተሳሰብ ተተካ። ‹‹የሕዝብን ገንዘብ ለግል ጥቅም ማዋል ወንጀል ነው›› የሚሉትን ሰዎች በጥይት እንደ ንፍሮ ቀቀሏቸው። እንደ ነፍሮ ከተቀቀሉት አንዱ በዓሉ ግርማ ነበር። ወንጀል ስለሰራ ሳይሆን፣ ‹‹በሕዝብ ስም ከሚነግዱ ኔጋዴዎች አብዮቱን ማጥራት ያስፈልጋል›› ብሎ ስለጻፈ ብቻ ነበር። ከበዓሉ ‹‹አንደበት›› እንስማ፡-

*‹‹…ለግል ጥቅማቸውና ፍላጎታቸው ሥልጣን የሚያሳድዱ ሰዎች በዘተዋል።…አደገኛ አዝማሚያ ነው—የተንኮል ገበያ ደርቷል። ከዚያ እንግዲህ ምናለ? መኪናና ቪላ ማማረጥ፥ ጥሩ መብላት፥ መጠጣት፡ መልበስ፥ መሽቀርቀር፥ በየዕለቱ የበሰለ ብርቱካን እየመሰሉ መሔድ—እንድያም ሲል ቆንጆ ቆንጆዎችን እያማረጡ ሕይወትን መቅጨት። በስልክ ሀሎ!*

*እያሉ ቤት ለምትፈልገው ቤት፥ ሥራ ለምትፈልገው ማለፊያ ሥራ፥ የደመወዝ ጭማሪ ለምትፈልገው ማለፊያ ጭማሪ። ተጠቅሞ መጥቀም፥ በለቶ ማብላት፥ ማብላትና መብላት። በሥልጣን እየተጠቀሙ ጥቅሞችን ለወደዱትና ለፈለጉት እንደ ጠበል መርከፍከፍ። ይህ ሁሉ እየታየ ነው። እኔ የምሰጋው በሕዝብ ስም ተነስተን ከሕዝብ እየራቅን—ለሕዝብ ባዳ እየሆን እንዳንሔድ ነው። ጥራት! ጥራት! በሕዝብ ስም ከሚነግዱ ኔጋዴዎች አብዮቱን ማጥራት ያስፈልጋል። ለግል ታርክ፥ ለግል ዝና ይበልጥ ስለምንጨነቅ ኀብረት ጠፍቶ ግላዊ ሩጫና ጀብደኝነት ይነግሳል።…እኔ ከጠላት ይልቅ በጣም የሚያሰጋኝ ይህ ነው››* (ኦሮማይ፣ ገጽ 298-299።)

መቸም ሆዳም ሰው እምብርት የለውም፣ ጅብ ነዋ! ሰውየው ‹‹ድንቁርናና ስልጣን ሲጋቡ ውጤቱ አደገኛ ነው›› ብሎ የተነበየው ነገር ለካስ ትክክል ነበር! አብዮታዊው መንግስት ለዘለዓለሙ ላይመለስ ተሰናብቶን የሄደው ከ25 ዓመት በፊት ነበር! ነፍሱን ይማር!

(2) በሌላ በኩል፣ ከ17 ዓመት የትጥቅ ትግል ቦኋላ የ‹‹እናውቅልሃለን›› ፖሊቲካዊ ፍልስፍና ከአብዮታዊው መንግስት ‹‹የተረከበው›› ልማታዊ መንግስት፣ ‹‹በሕዝብ ስም ከሚነግዱ ክራይ ሰብሳቢዎች ልማቱን ማጥራት ያስፈልጋል›› ብሎ ከተነሳ 25 ዓመታትን አስቀጥሯል። ከኢሕአዴግ ‹‹አንደበት›› እንስማ፡-

*‹‹የኪራይ ሰብሳቢነት ፖሊቲካዊ ኢኮኖሚ የበላይነት ባገኘበት አገር የመንግስትን ሥልጣን መቆጣጠር ከሞላ ጐደል ብቸኛው የመበልጸግያ መሣሪያ ይሆናል። ሥልጣኑን የያዘና ሥልጣኑን ከያዘው ጋር በቅርብ የተሳሰረው ሁሉ ኪራይ መሰብሰቡን በሰፊው በማስኬድ እንደሚከብርና መንግሥት ሁሉንም እንደ ልማት አስተዋጾኦ እኩል ማስተናገድ ሳይሆን እንደ ቅርበቱ የኪራይ መሰብሰብ ዕድል እንደሚከፍትለት ስለሚታወቅ ሥልጣን መቆጣጠር የሞትና የሽረት ጉዳይ ይሆናል።…ኪራይ ሰብሳቢነት የፖሊቲካ ትግሉ የአመለካከት ሳይሆን በዋናነት የኪራይ መሰብሰብ እድሎችን በሞኖፖል በመያዝ ወይም በመጋራት ጥያቄዎች ዙሪያ የሚከናወን ነው። የሰለጠነና የተረጋጋ ትግልና የሥልጣን ሽግግር ሳይሆን የኑሮ መሠረትን በመገንባትና በመከላከል ዙሪያ የሚከናወን ፍልሚያ የሚካሄድበት ዴሚክራሲ ይሆናል።…(ኢሕአዴግ፤* ልማት፣ ዲሞክራሲና አብዮታዊ ዲሞክራሲ፤ አድስ አበባ፣ 1999፣ ገጽ 83ff)

ከደኅረ ቅኝ-ግዛት አፊሪካ ፖሊተካዊ ፍልስፍና መነጽር ስንመለከት፣ የኢሕአዴግ አብዮታዊ ደሞክራሲ ለሀገራችን ኢትዮጵያ በአንፃራዊነት የተሻለ ነበር። ይሁን እንጅ፣ ኢሕአዴግ በሕዝብ ስም ከሚነግዱ ኔጋዴዎች ልማቱን ማጽዳት አልቻለም። ያለአግባብ መበልጽግ (ሙስና) ባህል ሆኗል፤ የመልካም አስተዳደር እጦት ሰፍኗል፤ የውሸት ባሕል ነግሷል፤ ለሆዱና ለፍትወት ብቻ ያደረ ትውልድ ተፈጥሯል፤ አድሏዊነት፣ ጥላቻ፣ ዘረኝነት፣ ጨቋኝነት ተንሰራፍቷል፤ ብሔርተኝነት ከመጠን በላይ ተለጥጧል፤ በሠላምና በፍቅር አንድ ላይ መኖር አልተቻለም፤ ሕዝብና መንግስት የጥይት ጨዋታ ውስጥ ግብቷል፤ ወጣቱ ተስፋ ቆርጧል፤ መግባባት፣ መደማመጥና መነጋገር ጠፍቶ መናናቅ ብቻ ሆኗል፤ የአብሮነት መንፈስ የሚባል ነገር ጠፍቷል፤ ለምዕራቡ ዓለም የአገብዳጅነት መንፈስ ሰፍኖ ሕዝቡ ስሜቱ ተሰለቧል፤ ደሃው በኋይልና በጉልበት ከተወለደበት ቀዬ ተፈናቅሏል፤ ወዘተ። በአጠቃላይ፣ እንደገና ተመልሰን የቆንጨራ ጨዋታ ውስጥ ገብተናል፤ ይህ የማይካድ ሐቅ ነው።

ዞሬም ቀረ፣ መንግስት በሕዝብ ብሶትና እንባ ማትረፍ የሚሹትን ሰዎች አያውቅም ማለት አይቻልም። ዝለዝህ፣ በሕዝብ ስም የራሳቸውን ኑሮ ያመቻቹና የሕዝብን ገንዘብ በጀንያ የምዘረፉት ግለሰቦችን ወደ ፍርድ ለምን እንደማያመጣቸው ፈጽሞ ግልጽ አይደለም። በአሁኑ ግዜ በሥርዓቱ ውስጥ ተሰግስገው ያሉ አብዛኞቹ ግለሰቦች (ሁሉም አይደሉም) ስለሆዳቸው እንጅ ስለሕዝቡ አሰቃቅ ሁኔታ የሚያስቡበት ሰዓትም የላቸውም። የሚከተለው የሞገስ ሃብቱ ግጥም የእነኘህን አድርባይ ግለሰቦችን የ‹‹እናውቅልሃለን›› ፖሊቲካዊ ፍልስፍና ውጤት በትክክል ይገልጻል የሚል ጽኑ እምነት አለኝ፡-

መቶ ሺህ ብር ይውጣ<br>
ሰው ጠግቦ እንድወጣ<br>
ውስኪም ብዙ ግዙ<br>
ቢራም ብዙ ብዙ<br>
ምግብም ብዙ ብዙ<br>
ሁሉም በገፍ ይምጣ<br>
ሰው ጠግቦ እንድወጣ<br>
እየበላህ ብላ፣ እየጠጣህ ጠጣ<br>
ከህዝብ ነው እንጂ ካንተ ኪስ አይወጣ

ይህ ነው እንግድህ ሰውየው ‹‹በሕዝብ ስም ተነስተን ከሕዝብ እየራቅን—ለሕዝብ ባዳ እየሆን እንዳንሔድ›› ያለው! ነፍሱን ይማርና የቀድሞ ጠቅላይ ምኒስተር መለስ ዜናዊ ‹‹የመንግስት ሌቦች እጅና እግራችንን አሰሩ›› ሲል፣ ‹‹መንግስት ሌባ እየሆነ መቷል›› ማለቱ ነበር እንጅ ሌላ ምስጥር የሌውም። መንግስት ሙስና የምሉት ካንሰር ሀገረቷን ከመግደሉ በፍት አስቀድሞ መድኃኒቱን ካለፈላለገለት መዘዙ አደገኛ መሆኑ አጠያያቅ አይደለም። በሕዝብ ስም እየነገዱ ከፈተኛ ሀብት ያካበቱትን ግለሰቦች እያጣራ ፍርድ ፍት የማቅረብ ሞራላዊ ግደታ አለበት። በሙስና ምክንያት 20 ሚሊዮን የናጠጠ ሀብታምና 80 ሚሊዮን መናጥ ድሃ ይዘን የሚንቀጥልበት ምንም ዓይነት መለኮታዊም ሆነ ምድራዊ ምክንያት ሊኖር አይገባም። ‹‹በቅርብ ጊዜ ውስጥ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ እንሰለፋለን›› የሚል ትንቢት ግቡን እንድመታ ከተፈለገ፣ መንግስት የሙሰኞች እጅ እንዴት መቀንጠስ እንዳለበት ከአሁኑ በደንብ ልያስብበት ይገባል! ይህ እስካልተደረገ ድረስ፣ ‹‹መጀመሪያ ሙስና ነበረ፣ ሙስናም በስልጣን ዘንድ ነበረ፣ ሙስናም ስልጣን ነበረ›› የሚል ‹‹የሙስና ወንጌል›› በኢትዮጵያ ምድር እየሰተበከና እየተተገበረ ይቀጥላል!

ባለፉት 42 ዓመታት፣ ፖሊቲካዊና ማኀበራዊ ችግሮቻችንን በጨረጰዛ ዙሪያ መፍታት አልተቻለም፤ 17 ስደመር 25 ይሆናል 42! እንደ አንድ ወጣት ዜጋ ግራ ገብቶኛል! የ‹‹እናውቅልሃለን›› የፖሊቲካዊ ፍልስፍና ከጥይት ጨዋታ ወደ ጨረጰዛ ዙሪያ ማምጣት አልተቻለም። ችግሮች ስፈጠሩ ሰላም እንድወለዱ የሚያስችሉ ባህል የለንም። ከዝህ በፊት በግልጽ ለማስቀመጥ እንደሞከርኩት፣ በባሕልና በታሪክ በተሳሰሩ ሕዝቦች መካከል የቆንጨራ ፍልስፍናን ማቀንቀን፣ ለዝች ሀገር የሚበጅ አይመስለኝም። ግን ምን ያረጋል! አሁን በተጨባጭ እየሆነ ያለውን ነገር ስመለከት፣ ‹‹ኦሮማይ›› እንድል አስገድዶኛል። ዳግም ወደ እርስ በርስ ጦርነት እንዳንገባ ትልቅ ስጋት አለኝ።

ዝለዝህ፣ ምሁራን፣ የሀገር ሹማግለዎችና የሃይማኖት አባቶችን ከባድ የቤ-ሥራ ይጠብቃቸዋል። በተለይ፣ የሃይማኖት አባቶች ትልቅ ኋላፍነት አለባቸው! ሕዝቡ በቆንጨራ እየተጨራረሰ ዝም የሚትሉ ከሆነ፣ በፈጣሪና በሕግ ፊት ተጠያቅዎች ናችው። እምነትና ፀሎት ብቻ በቂ አይደለም። ሰይጣንም እኮ እግዚአብሔር የዘለዓለም ኗር መሆኑንና ታላቅ አምላክ መሆኑን ያምናል። ግን መልካም ሥራ የለውም፤ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው! የኀይማኖት አባቶች ሆይ! ‹‹አድስ አማኝ ከጳጳሱ በላይ ለበቴክርስቲያን ተቆርቋር ነው›› እንደማትሉኝ ተስፋ አለኝ። ምንም ዓይነት መልካም ሥራ ሳይኖረው ያንን ለማለት የሚደፍር የእግዝብሔር አገልጋይ ካሌ ግን፣ ‹‹ፂም በማሳደግ ቢሆን ፍየል ትሰብክ ነበር›› የሚል ተመጣጣኝ ምላሽ ሰለሚሰነዝር ላንደማመጥ እንችላለን! ይልቅ፣ በልጅነት መንፈስ እናንተን ማሳሰብ የፈለኩት ነገር ቢኖር፣ ፍትሕ ስጓደል አይታችው ዝም አትበሉ ነው። የእግዝብሔር ቃልም የሚላችው ይህንኑ ነውና፤

*“ዓመት በዓላችሁን ጠልቼዋለሁ ተጸይፌውማለሁ፤ የተቀደሰውም ጉባኤአችሁ ደስ አያሰኘኝም። የሚቃጠለውን መሥዋዕታችሁና የእህሉን ቍርባናችሁን ብታቀርቡልኝም እንኳ አልቀበለውም፤ ለምስጋና መሥዋዕት የምታቀርቡልኝን የሰቡትን እንስሶች አልመለከትም።የዝማሬህንም ጩኸት ከእኔ ዘንድ አርቅ፤ የመሰንቆህንም ዜማ አላደምጥም። ነገር ግን ፍርድ እንደ ውኃ፥ ጽድቅም እንደማይደርቅ ፈሳሽ ይፍሰስ።” (አሞጽ 5፤ 22-24)*

ይህ ማለት፣ አንድም፣ የሚተሰብከውን ኑር እንጅ፣ ፈሪሳዊ አትሁን፤ ሁለትም፤ «ከመጠምጠም መልካም-ሥራ ይቅደም» ማለት ነው። ከምሁራንና ከሀገር ሹማግለዎችም ተመሳሳይ ተልዕኮ እንጠብቃለን፤ ተማርኩ ብሎ ጠሩንባ መንፋት በቂ አይደለም፤ ትልቁ ነገር ዕውቀትን ወደ ተግባር መቀየሩ ነው! የአስተሳሰብ ለውጥ ሳይኖር ተማርኩ ብሎ መንጠራራት፣ በፍልስፍው ዓለም ምሑራዊ ውስልትና ወይም የአስተሳሰብ ሽርሙጥና ይባላል!

በመጨረሻም፣ መንግስትና ሕዝብ ከታረቁ ብሔራዊ እርቅ ላይ እንደርስ ይሆናል፤ ካልሆነ መበታተናችን ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው።ከማንኛውም እልቅት ፈጣሪ እንድጠብቀን ግን አጥብቀን መሥራት አለብን። ከሁሉም በላይ፤ ለዝች ሀገር የሚያስፈልጋት ሠላም ነው፤ ሠላም! ሠላም! ሠላም! ዘላቅ ሠላም! ሮናልድ ሬገን ያለውን ግን እንዳንረሳ «ሰላም የግጭት አለመኖር አይደለም፤ ግጭትን በሰላማዊ መንገድ የመፍታት አቅም ነው፡፡» ስለዝህ፣ ከራሷ ጋራ ሠላም የፈጠረች ኢትዮጵያን ለመፍጠር በአንድነት እንስራ። ማርቲን ሉተር ኪንግ እንደሚለን «ጦርነትን ማወጅ የለብንም ማለት ብቻ በቂ አይደለም፤ ሠላምን መውደድና መስዋዕትነት መክፈልም ይኖርብናል፡፡› መንግስትና የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ! ስስታምነት ይብቃን፤ የንጹሐን ደም መፍሰስ የለበትም፤ አድሏዊነትን አጥብቀን እንዋጋ፤ ሰውን በሰውነቱ ብቻ እናከብር፤ የመጠላለፍ ፖሊቲካ ይብቃን፤ ሁሉም ነገር እኮ አለን—ሀገራችን ኢትዮጵያን ምን ጎደላት? ምንም! ግን አንድ የጐደለን ነገር አለ፤ መተሳሰብ፤ መቻቻል፤ መፈቃቀር፤ አንድነት፤ ደግነት ወዘተ። አዎን! እሱ ነው የጐደለን! የእኛ ጥረት ተጨምሮበት የጐደለውን ነገር የመሙላት አቅም ያለው አንዱ ፈጣሪ ብቻ ነው፤ እናም ፈጠሪ እያንዳንዳችንን ይርዳን። በሃይለመለኮት መዋእል ግጥም ልሰናበታችው!

ምን ጠቀመዉ ቃየል—የመሳሪያ ቋንቋ<br>
ሰጠመ ጠፋ እንጂ—ባቤል ደም አረንቋ

መኢኑም አባተ—ሰመረ መረሳ
ኦቦንግ አብዱል ከሪም—ጋቸኖ ቶሎሳ
አብረኸት ምንትዋብ—ኛዳከም ጋዲሴ
በላህ በነብዩ—በሶስቱ ስላሴ
ሰይፉም ዶማ ይሁን—ሞርተሩም አንካሴ

ምንጭ፡- ዮሴፍ ሙሉጌታ ባባ፣ የኢትዮሮፒያንስ የአስተሳሰብ ቅሬ፣ ገጽ. 67-70

*Yoseph Mulugeta Baba can be reached at: kankokunmalimaali@gmail.com